# የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 848/2014

Directive for the Administration of Civil Society Fund
(Directive No. 848/2014)


የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ሰርቪስ ድርጅቶች ባለስልጣን
F.D.R.E Authority for Civil Society Organizations



ጥቅምት 26፥ 2014

# የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ

## (ቁጥር 848/2014)

### የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ
### (ቁጥር 848/2014)

### Directive for the Administration of Civil Society Fund Directive
### (No. 848/2021)

በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ አንቀፅ 86 መሰረት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የሚተዳደር የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ እንደሚቋቋምና ባለሥልጣኑም ይህንኑ በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ እንደሚያወጣ በመደንገጉ፤

Whereas, a Civil Society Fund that is to be administered by the Authority for Civil Society Organizations is to be established and a detailed directive concerning the Fund is to be issued by the Authority pursuant to Article 86 of the Civil Society Organizations Proclamation;

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የሲቪል ማህበረሰቡን በፋይናንስ ለመደገፍና በዘርፉም ያላቸውን አስተዋፅኦ ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ምቹ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it is imperative for the Authority for Civil Society Organizations to support the Civil Society Organizations financially and to promote their contribution in the sector to a higher level;

ፈንዱ በአዋጁ የታለመለትን በጎ ፈቃደኝነትንና የዘርፉን እድገት የማበረታታት አላማ በሚገባ እንዲወጣ ፈንዱ የሚተዳደርበትን ሁኔታ በዝርዝር ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it is necessary to issue a directive that outlines the details of the Fund's administration in order for the Fund to meet its objectives of encouraging volunteerism and promoting growth;

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 18 እና በአዋጁ አንቀፅ 86 ንዑስ አንቀፅ 5 እና በአንቀጽ 89 (2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

Now therefore, The Authority for Civil Society Organizations has, in accordance with Articles 6 sub-article (18), Article 86 sub-article (5), and Article 89 sub-article (2) of the Proclamation, issued this directive.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 848/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "አዋጅ" ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው፤

2) "ፈንድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ (2) የተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ ነው፤

3) "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 እና በፌዴራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 በተደረገው የስያሜ ማሻሻያ የተቋቋመው "የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን" ነው፤

4) "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ማለት ነው፤

## Part One

## General

### 1. Short Title

This Directive can be cited as the "Administration of Civil Society Fund Directive No.2/2021"

### 2. Definitions

In this Directive, unless the context so requires:

1. "Proclamation" shall mean the "Civil Societies Proclamation No. 1113/2019";

2. "Fund" shall mean the Civil Society Fund established pursuant to Article 86 sub-article (2) of the Proclamation.

3. "Authority" shall mean the "Authority for Civil Society Organizations" that was established pursuant to Article 4 of the Proclamation & accorded change of name in accordance to definition and duties of the executive organs of the federal government proclamation No. 1263/2021.

4. "Director-General" shall mean the Director-General of the Authority for Civil Society Organizations.

5) “በጎ ፈቃደኝነት” ማለት አንድ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ተቋም ያለምንም የገንዘብ ጥቅም እና በማህበራዊ አገልግሎት ሌሎችን ለመጥቀም ሲባል ግዜውን፥ ክህሎቱን፥ ልምዱን ወይንም እውቀቱን የሚያካፍልበት ተግባር ነው፤

6) “ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች” ማለት አጠቃላይ ማህበረሰቡ ካለበት የኑሮ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ለማህበራዊ መገለል ወይም ለድህነት ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ህፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ሴቶች፣አረጋውያን፣ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ ማህበረሰቦችን፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው፣ ሴተኛ አዳሪዎች፣ በአደንዛዥ እጽ ተፅዕኖ የደረሰባቸው እና የአዕምሮ ጤና ችግር ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካትታል፡፡

5. “Volunteerism” shall mean the practice of providing an individual’s or group’s time, skills, and experience for the benefit of others without the expectation of financial benefit;

6. “Members of the community that need special support” shall mean members of the community who are highly vulnerable to social exclusion or poverty as compared to the living conditions of the general community and shall include, for the purposes of this directive, children, persons with disabilities, women, elderly people, persons displaced from their place of residence, persons who are HIV positive, commercial sex workers, and persons with mental illnesses.

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የሲቪል ማህበረሰብ ፈንዱ ተጠቃሚ በሆኑ ወይም በፈንዱ ተጠቃሚ ለመሆን ማመልከቻ በሚያስገቡ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3. Scope of Application

This Directive shall be applicable to the beneficiaries of the Civil Society Fund or organizations that submit applications to be beneficiaries of the Fund.

## ክፍል ሁለት
## የፈንዱ አላማና አደረጃጀት

### 4. የፈንዱ አላማዎች

የሲቪል ማህረሰብ ፈንድ ባለሥልጣኑ ባለው ውስን የፋይናንስ አቅም ላይ የሚመሰረት አነስተኛ የፋይናስ ወይም የፕሮጀክት መሳሪያዎች ድጎማ ነው፡፡ በዚህ ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባለሥልጣኑ ተመዝጋቢ የሆኑ አገር በቀል ሲቪል ማህበራት ብቻ ሲሆኑ ፈንዱ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፤

1) በጎ ፈቃደኝነትንና የዘርፉን ዕድገት ማበረታታት፤
2) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አገራዊ አስተዋፅዖ ማበረታታት፤
3) ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶችን ማበረታታትና ማገዝ፡፡

### 5. የፈንዱ መርሆዎች

ፈንዱ በሚከተሉት ዋና ዋና መርሆዎች የሚመራ ይሆናል

1. ግልፀኝነት፤
2. አሳታፊነት፤
3. እኩል እድል መስጠት፤
4. ተጠያቂነት፤
5. ውጤታማነት፤

## Part Two
## Objectives and Organization of the Fund

### 4. Objectives of the Fund

The Civil Society Fund is established to subsidize Organizations by way of small financial assistance or program tools within the limited financial resources of the Authority. The Fund, the beneficiaries of which shall be indigenous Organizations that are registered with the, shall have the following objectives:

1. To promote volunteerism and the growth of the sector;
2. To promote the national contribution of Civil Society Organizations and;
3. To encourage and support Organizations working with Members of the Community Needing Special Support.

### 5. Principles of the Fund

The Fund shall be managed in accordance with following principles:

1. Transparency;
2. Being participatory;
3. Giving equal opportunity;
4. Accountability;
5. Effectiveness;

6. ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ወይም ተጠቃሚዎችን መሰረት ማድረግ፤
7. ተዓማኒነት፡፡

6. Being need- or beneficiary-based; and
7. Trustworthiness

## 6. የፈንዱ አደረጃጀት

1. ባለሥልጣኑ ፈንዱን የሚያስተዳድር የሥራ ክፍል ያደራጃል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ የቴክኒክ ኮሚቴ ሊያዋቅር ይችላል፤
3. የቴክኒክ ኮሚቴ አባላቱ በሚከተለው መልኩ የሚዋቀሩ ይሆናል፤
   (ሀ) ከበጎ ፈቃድ ማጎልበትና ፈንድ አስተዳደር የሥራ ክፍል የሚወከል አንድ ኃላፊ ሰብሳቢ፤
   (ለ) የፈንድ አስተዳደር ቡድን መሪ -------ጸሃፊ፤
   (ሐ) ከጤና ሚኒስቴር----አባል፤
   (መ) ከትምህርት ሚኒስቴር-----አባል፤
   (ሠ) ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር---አባል፤

## 6. Organization of the Fund

1. The Authority shall organize a department that will administer the Fund.
2. Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Authority may appoint a Technical Committee that is comprised of members from different bodies.
3. The Technical Committee shall be composed of:
   a) A manager from the department of “Volunteerism Promotion and Fund Administration” Chairperson;
   b) Fund Administration Team Leader - Secretary;
   c) A representative from the Ministry of Health - Member;
   d) A representative from the Ministry of Education - Member:
   e) A representative from the Ministry of labour and skills- Member;

(ረ) ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር----አባል፤

(ሰ) ከአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን-------አባል፤

(ሸ) ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት -----አባል፤

4. የባለሥልጣኑ የበጎ ፈቃድ ማጎልበትና ፈንድ አስተዳደር የስራ ክፍል ለቴክኒክ ኮሚቴው በጽሕፈት ቤትነት ያገለግላል፤

5. የቴክኒክ ኮሚቴው በዚህ መመሪያና አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ፕሮፖዛሎችን በመገምገም ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፤

6. የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከቴክኒክ ኮሚቴው የውሳኔ ኃሳብ በመነሳትና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔዎችን ይወስናል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው የበጎ ፍቃድና ፈንድ አስተዳደር የስራ ክፍል አመታዊ እቅዱን በሚያወጣበት ወቅት ለአካል ጉዳተኞችና ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ

f) A representative from the Ministry of Women and social affairs - Member;

g) A representative from the Disaster Risk Management Commission – Member;

h) A representative from the Civil Society Organizations' Council – Member.

4. The Authority's Department of Volunteerism Promotion and Fund Administration shall serve as the Fund's Secretariat.

5. The Technical Committee shall evaluate proposals in accordance with this Directive and other relevant laws, and make recommendations to the Director-General.

6. The Director-General shall make decisions on the basis of the Technical Committee's recommendations and by taking other factors into consideration.

7. The Department of Volunteerism Promotion and Fund Administration mentioned in sub-article (1) above shall, in its annual planning process, especially include plans for the benefit of persons with disabilities

ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ዕቅዶችን በልዩ ሁኔታ ማካተት ይኖርበታል፡፡

and other Members of the community that need special support.

## 7. የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባራትና ኃላፊነት

## 7. Powers and Responsibilities of the Civil Society Fund Technical Committee

የቴክኒክ ኮሚቴው ዋና ኃላፊነት በመምረጫ መስፈርቱ መሰረት ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን መገምገምና ለውሳኔ የሚሆን ኃሳብ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ነው፤ በዚህም መሰረት የቴክኒክ ኮሚቴው ፈንዱን በተመለከተ በተለይም፤

1. ስለፈንዱ አደረጃጀት፣ አሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ አጠቃቀም፣ የፈንድ ጥያቄዎች ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ባለሥልጣኑን ያማክራል፤
2. በፈንድ አስተዳደሪው ኃላፊ የሚቀርቡለትን የፈንድ ጥያቄዎች ከፍትሃዊነት፣ከአሳታፊነት፣ግልጸኝነትና ሌሎችም ሁኔታዎች አኳያ በመመርመር ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

The main responsibility of the Technical Committee is to evaluate proposals based on its selection criteria in a fair and democratic manner and make recommendations to the Director-General.

Accordingly, it shall, specifically in matters concerning the Fund:

1. Consult the Authority regarding the Fund’s organization, collection, administration, utilization, application-processing, and other related matters.
2. Make recommendations to the Director-General after reviewing fund applications from the perspective of justice, participation, transparency and other particulars presented to it by the manager of the Fund.

## 8. የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ቴክኒክ ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመን

## 8. Term of Service of Technical Committee Members

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚዋቀረው የቴክኒክ ኮሚቴ

1. The members of the Technical Committee appointed according to Article 6 sub-article (3) shall serve in the committee for one year as

አባላት ለአንድ አመት እንዲያገለግሉ ከሚመጡበት ተቋም የሚወከሉ ይሆናሉ፤

2. ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም አንድ አባል በሚወክለው ተቋም ፍቃደኝነት መሰረት ከአንድ አመት በላይ በቴክኒክ ኮሚቴው አባል ሆኖ ሊሰራ ይችላል፡፡

representatives of their respective organizations.

2. Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a member may serve in the Committee for a period longer than one year upon the consent of the organization it represents.

## 9. የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ሙያዊ ስራ አካሄድ

የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ፤

1. ሚስጢር ጠባቂ፤
2. በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ የሚሰሩ፤
3. ገለልተኛ ሆነው የተሠጣቸውን ስራ በብቃት የሚወጡ፣
4. በዲሲፕሊን የታገዙና በስብሰባዎች ላይ ሳያቋርጡ የሚሳተፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
5. ከላይ ከቁጥር 1 እስከ 4 የተዘረዘሩትን ሙያዊ አካሄዶችንና ሌሎች የአሰራር ስርዓቶችን የሚጥሱ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት መኖራቸው በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሲታመንበት ዋና ዳይሬክተሩ በሌላ አባል እንዲተኩ ለሚመለከተው ተቋም በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡

## 9. Ethical Standards of Technical Committee Members

The members of the Civil Society Fund Technical Committee shall:

1. Adhere to the principle of confidentiality;
2. Discharge their duties with utmost sense of responsibility;
3. Competently undertake their work in an independent manner;
4. Be disciplined and continually participate in meetings;
5. Where the Director-General is convinced that there are members of the Committee that have failed to meet the standards laid out under sub-articles (1) – (4) above and who violate other working procedures, he shall request, by letter, that the organizations represented by such members to replace them.

## 10. የቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ ስነ ስርዓት

1. ኮሚቴው በሁለት ወር አንድ ግዜ ይሰበሰባል። ሆኖም በፈንድ አስተዳደር

## 10. Meeting Procedure of the Technical Committee

1. The Committee shall convene once every two months. However, it may hold

ኃላፊው ጥሪ የቴክኒክ ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባዎች በማንኛውም ግዜ ሊያደርግ ይችላል፤

2. ከቴክኒነክ ኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል፤

3. የቴክኒነክ ኪሚቴው ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት በድምፅ ብልጫ ይወሰናል። ሆኖም ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

4. የቴክኒክ ኪሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የራሱን የስብሰባ ስነስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የፈንዱ ተጠቃሚዎችን ስለመወሰን

### 11. የፈንዱ ተጠቃሚ ሲቪል ማህበራት ስለሚመረጡበት መስፈርቶች

ይህ ፈንድ በዋነኛነት የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ለማጠናከርና ባህል ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፍ ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ በሲቪል ማህበራት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በበጎ ፍቃድና በጎ አድራጊነት ዙሪያ የሚያተኩሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለሥልጣኑ የፈንድ ተጠቃሚን የሚከተሉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ይመርጣል፤

1. አገር በቀል ድርጅት መሆን፤

2. ድርጅቱ ያቀረበው ፕሮፖዛል አንድ ከተለየ ወይም ከተለዩ የመንግስት ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ጋር ያለው ቁርኝት እና ተደጋጋፊነት፤

extraordinary meetings upon call by the manager of Fund Administration.

2. More than half of the members of the Committee present for a meeting shall constitute a quorum.

3. Decisions shall be passed by a simple majority of the votes of Committee members present. If the vote is tied, the chairperson shall have a casting vote.

4. The Committee may set its own meeting procedures at any time where it finds it necessary to do.

## Part Three
## Determining the Beneficiaries of the Fund

### 11. Criteria for Selecting Fund Beneficiaries

The projects proposed by Organizations shall focus on voluntary and charitable services as The Fund aims mainly to promote the culture of volunteerism and to support the existing effort in this regard. The Authority shall employ the following criteria to determine the beneficiaries of the fund:

1. Being an indigenous organization;

2. Alignment of the organization’s proposal with a specific strategic direction(s) of the government;

3. ምርጥ ተሞክሮ ላይ መሰረት ያደረገና ገንዘቡን በሚገባ ሥራ ላይ የሚያውለው መሆኑ፤
4. በፕሮፖዛሉ የቀረበው ሀሳብ አዲስ ፈጠራና አካሄድን መሰረት ያደረገ መሆን፤
5. በፕሮፖዛሉ የቀረበ ሀሳብ አዳዲስ የስራ ዕድሎችን የሚፈጥርና በተጨባጭ የሚታይ ችግርን የሚፈታ መሆን፤
6. ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሰብዓዊ መብት ማሰከበርና ማረጋገጥ ዙሪያ የሚሰሩ ሲቪል ማህበራትን ለማበረታታት ባለሥልጣኑ ከፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይችላል፡፡

3. Being based on the best practice and the prospect of properly utilizing the funds toward the proposed end;
4. Novelty of the concept and methodology of the proposal; and
5. Creating new employment opportunities and tackling actual issues in a tangible manner.
6. Without prejudice to the foregoing criteria, the Authority may facilitate for Organizations that work in the area of human rights assurance and protection to benefit from the Fund with the purpose of encouraging their work.

## 12. ለፈንዱ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

አንድ ድርጅት የፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን ቢያንስ የሚከተሉትን ቅድመሁኔታች ሊያሟላ ይገባል፡፡

1. ግልፅ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የፋይናንስ እና ግዢ አስተዳደር የሚከተል መሆኑ፤
2. በፕሮፖዛሉ የተጠቀሰውን ፕሮጀክት የሚፈፅምበት ሌላ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሌለው መሆኑ፤

## 12. Eligibility

An organization has to fulfil the following requirements to benefit from the Fund:

1. Having a transparent system of decision-making, financial and procurement administration;
2. Not having another reliable source to implement the proposed project;

3. የተቋሙ አጠቃላይ ድርጅታዊ ዳራ ድርጅቱ በባለሥልጣኑም ሆነ በመንግስት የሚወጡ አዋጆችና መመሪያዎች አክብሮ ስለመንቀሳቀሱ አመላካች መሆን ፤
4. አሳማኝ የፕሮጀክት አፈጻጸም ዕቅድ መኖርና ፕሮጀክቱን ለመፈጸም የሚያስችል በቂ ሰው ሀይልና ተቋማዊ አቅም የገነባ መሆን፤
5. የፕሮጀክቱ ጭብጥ በተገቢ መልኩ በተከናወነ የችግር ዳሰሳ ላይ የተመሰረተ አሳማኝ ዓላማና ምክንያታዊነትን መሰረት ያደረገ መሆን፤
6. የፕሮጀክቱ አቀራረጽ በተለይም ከመንግስት ስትራቴጂዎችና እና እቅዶች ጋር የተናበበ፣ ቅንጅታዊ አሰራርን መሰረት ያደረገ እና ዘላቂነትን የሚያረጋግጥ መሆን፤
7. ፕሮጀክቱ ግልጽ እና አሳማኝ የክትትል፣ ድጋፍ እና መማማሪያ ስርዓት እንዳለው የሚያሳይ የክትትልና ድጋፍ እቅድ መኖር፤
8. የበጎ ፍቃድ ማጎልበትና ፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ዝርዝር የመምረጫ መስፈርቶችና የውጤት አሰጣጥ ስርዓት አዘጋጅቶና

3. The background of the Organization indicating that it complies with all the Authority's Directives and other laws of the government;
4. Having a convincing project implementation plan; sufficient manpower and organizational capacity to implement the project;
5. The theme of the project having its purpose based on an appropriately conducted problem survey and good reason;
6. The project design being particularly aligned with government strategies and plans, having an integrated approach to implementation and ensuring sustainability;
7. A monitoring and support plan showing that the project has a reliable monitoring, support and learning system;
8. The Volunteerism Promotions and Fund Administration Director shall, by taking into account the above criteria, develop a system with detailed selection criteria and scoring rubric, have it approved by the

በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አጸድቆ ፤የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በይዘትና በፋይናንስ አቀራረብ መሰረት አወዳድሮ የሚመርጥ ይሆናል፡፡

Director-General, and select project proposals on the basis of content and financial offering.

## 13. ለፈንዱ የሚቀርብ ማመልከቻ ይዘት

## 13. Contents of Application

1. ማንኛውም ድርጅት ለፈንዱ የሚያቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

   (ሀ) የድርጅቱን ዝርዝር እቅድ የሚያሳይ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ጉዳዮችን ያካተተ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤

   (ለ) አስቀድሞ የተቋቋመና ከሌሎች ለጋሾች ገንዘብ ያላገኘ ድርጅት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

   (ሐ) ማመልከቻውን ከሚያቀርብበት አመት በፊት የተዘጋጀ አመታዊ የክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት፤

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተደነገገው ቢኖርም የተለየ፣ በተጨባጭ ችግሮችን ሊፈታ የሚችልና አዲስ የፈጠራ ሀሳብን መሰረት ያደረገ የፕሮጀክት ሀሳብ ለሚያቀርብ አዲስ የተቋቋመ ድርጅት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በልዩ

1. An application by an organization requesting to make use of the Fund shall include the following:

   a) A project proposal detailing the plans of the organization including technical and financial matters;

   b) A document evidencing that the application is made by an already-existing organization that has not previously received funding from donors;

   c) Annual activity and budget reports prepared for the budget year preceding the year in which the application is made.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, the Director-General may, under special circumstances, grant use of the Fund to a newly established organization that submits a proposal containing

ሁኔታ የፈንዱ ተጠቃሚ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።

**14. የፈንድ ማመልከቻ ጥሪ የሚደረግበት መንገድ**

1. በዚህ ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲቪል ማህበራት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው ግልጽ የፕሮፖዛል መቀበያ ጥሪ መሰረት የሚወዳደሩ ይሆናል፤
2. ባለሥልጣኑ የሚያስተላልፈው ጥሪ ሰፊ ሽፋን ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን፣ በባለሥልጣኑ ድረገፅ፣ በድርጅቶች ህብረት አማካኝነት ወይም በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች ይፋ ይደረጋል፤
3. ባለሥልጣኑ የፕሮፖዛል ጥሪ ማስታወቂያዎችን በቋሚነት ይፋ የሚያደርገው በበጀት አመቱ መጀመሪያ ባሉት ሶስት ተከታታይ ወራት ውስጥ ማለትም ከ ሃምሌ እስከ መስከረም ወር ይሆናል፤
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ቢኖርም ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፈንዱ ድጋፍ የሚሆን በጀት በተገኘበት በማንኛውም ጊዜ ጥሪ ሊያደርግ ይችላል፤
5. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቅድመ ሁኔታ ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ማለትም አደጋ

innovative methods and with the prospect of providing tangible solutions to problems.

**14. Call for Applications**

1. Organizations that are to benefit from the Fund shall compete on the basis of a clear call for proposals made by the Authority.
2. The Authority's call for applications shall be made via mass media that have a large audience, the Authority's website, consortia of organizations, and other similar means.
3. These calls shall be made regularly during the first three months of the budget year, from July to September.
4. Notwithstanding sub-article (3) above, the Authority may, if it finds it necessary to do so, make calls at any time where budget supporting the fund is obtained.
5. Notwithstanding the pre-conditions laid down in this Article, the Authority may, without making official calls,

በሚያጋጥምበት ጊዜ፣ የሚደረገው የበጀት ድጋፍ አነስተኛ ሲሆንና ጨረታ የማውጣትና የመገምገም ሂደት የሚወስደው ጊዜ እና የሚያስወጣው ወጪ ከሚደረገው ድጋፍ ጋር የማይመጣጠን ሲሆን፣ በወቅታዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነትና ሌሎችም አሳማኝ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይፋዊ ማስታወቂያ ሳያወጣ ለአንድ የተለየ ድርጅት ከፈንዱ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፤

give financial support from the Fund to one particular organization by taking into account the need of the current state of affairs and other reasonable factors. This is to be done under exceptional circumstances such as the occurrence of an emergency, where the budget support is low and the cost and time of launching tenders and evaluating bids is incommensurate to the budget support and the time available under the circumstances.

6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 የሚሰጥ ውሳኔ በባለሥልጣኑ በሚቋቋም ኮሚቴ የውሳኔ ኃሳብ መሰረት ዋና ዳይሬክተሩ የሚያፀድቀው ይሆናል፤

6. The decision under sub-article (4) above shall be made on the basis of a recommendation by a committee to be appointed by the Authority and the approval of such recommendation by the Director-General.

7. መስፈርቱን አሟልተው ከፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ የሲቪል ማህበራት ዝርዝር የባለሥልጣኑን ድህረ ገጽ ጨምሮ ሌሎች የማሳወቂያ አማራጮችን በመጠቀም ይፋ ይደረጋል::

7. The list of organizations that fulfil the criteria and become beneficiaries of the Fund shall be made public via the Authority’s website and other alternatives.

## 15. መንግስት ለፈንዱ ድጎማ የሚያደርግበት ሁኔታ

## 15. Contribution by the Government

1) ባለሥልጣኑ ፈንዱን ለማጠናከር ከባለሥልጣኑ መደበኛ በጀትና ከፈረሱ ድርጅቶች ከሚገኝ ገቢ በተጨማሪ

1. The Authority may, with the view of strengthening the Fund, support organizations by having government program budget earmarked and

በመንግስት የፕሮግራም በጀት በማስያዝና በማስጸደቅ የሲቪል ማህበራትን መደገፍ እንዲሁም ከገንዘብ ድጋፍ ባሻገር የሲቪል ማህበራትን የአፈጻጸም አቅም ማጎልበት ስራን ይሰራል፤

2) መንግስት ለፈንዱ የሚያደርገው ድጎማ የሚተላለፍበት መንገድ በመንግስት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፤

## 16. የክትትልና ግምገማ ስርዓት

1. ባለሥልጣኑ የፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ የሲቪል ማህበራት ተከታታይነት ባለው መልኩ በተቀመጡ ግቦች መሰረት ተግባራት እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ከባለሥልጣኑ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ጋር በማስተሳሰር ክትትል ይደረጋል፣ ሙያዊ እገዛ እና ድጋፍ ያደርጋል፤

2. ባለሥልጣኑ ፈንዱ ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉን ሲያጋግጥና በፈንዱ አጠቃቀም ዙሪያ ሌሎች የህግና የአሰራር መርህ ተላልፈው የተገኙ ድርጅቶች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## 17. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሂደት

1. በባለሥልጣኑ ፈንድ አስተዳደር ዙሪያ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የሲቪል

approved in addition to its regular budget and income from dissolved organizations. It shall also provide support to improve the implementation capacities of organizations.

2. The subsidies of the government to the Fund shall be transferred according to the finance directives of the same.

## 16. Monitoring and Evaluation

1. The Authority shall provide professional assistance and support to beneficiary organizations, and monitor that the activities of these organizations are undertaken according to successive goals by linking them to its system of monitoring and evaluation.

2. Where the Authority confirms that the funds are not being utilized to the designated ends and the existence of other violations of legal and procedural principles, it shall take the necessary action against organizations failing to comply with them.

## 17. Grievance Procedure

1. Any organization that has a grievance in relation to the Authority's management of the Fund may submit

ማህበረሰብ ድርጅት የፈንድ ተጠቃሚ ድርጅቶች ዝርዝር ይፋ በተደረገ 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቴክኒክ ኮሚቴው በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፤

a formal grievance complaint to the Technical Committee within five (5) working days after the Authority has made the list of beneficiary organizations public.

2. የቴክኒክ ኮሚቴው ቅሬታ በቀረበለት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው የጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፤

2. The Technical Committee shall respond to the complaint in writing within five (5) working days of receipt.

3. በቴክኒክ ኮሚቴው ውሳኔ እና ማብራሪያ ላይ ቅሬታ ያለው ድርጅት የቴክኒክ ኮሚቴው ውሳኔ በደረሰው 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

3. An organization that is not satisfied with the decision and explanation of the Technical Committee may submit its complaint to the Director-General within ten (10) working days of receiving the response.

4. በዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ድርጅት ቅሬታውን በአስር ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ቦርድ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

4. An organization that is not satisfied with the decision of the Director-General may lodge its complaint to the Authority's Board.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Four
## Miscellaneous Provisions

### 18. በባለሥልጣኑ ይዞታ ስር የሚገኝ ንብረት ወደፈንዱ የሚተላለፍበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከፈረሱ ድርጅቶች የተገኘ በባለሥልጣኑ ይዞታ ስር የሚገኝ ንብረትና ገንዘብ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን አንስቶ ወደ ፈንዱ ይተላለፋል።

### 18. Transfer of Assets to the Fund

Funds and assets in the Authority's possession and which were obtained from organizations that were dissolved before the issuing of this Directive shall be transferred to the Fund from the date this Directive is approved.

### 19. የባንክ ሂሳብ

ባለሥልጣኑ ለፈንዱ የተለየ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤

### 19. Bank Account

The Authority shall open a designated bank account for the Fund.

20. ኦዲት

የፈንዱ ሂሳብ አስተዳደር በየዓመቱ በዋና ኦዲተር የሚመረመር ይሆናል፡፡

21. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመ በኋላ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለሥልጣኑ ድህረገጽ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ጂማ ዲልቦ ደንበል
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

**20. Audit**

The financial administration of the Fund shall be examined by the Auditor-General each year.

**21. Amendment**

The Authority may amend this directive at any time.

**22. Effective Date**

This Directive shall enter into force on the day it is publicized by the Authority's website after registered by Ministry of Justice and signed by the Director General of the Authority.

**Jima Dilbo Denbel**
**Director-General**
**Authority for Civil Society Organizations**

**November 6, 2021**